


# አድቬር ዲስከስ

Advair Diskus@ (Fluticasone with Salmeterol)

## አድቬር ምንድነው?

አድቬር **ለአስም እና ሲኦፒዲ** ታማማሚዎች በቀላሉ ለመተንፈስ እንዲረዳቸው የሚታዘዝ መድሃኒት ነው። የተዘጉ የአየር ቧንቧዎችን የሚከፍቱ ሁለት መድሃኒቶች፤ ማለትም **ሳልሜትሮል እና ፍሉቲካሶል** የተባሉ መድሃኒቶች ይይዛል። አድቬር በተለያዩ መልኩ ይመረታል። አድቬር ኤርዱዎ፤ አድቬር ሪስፒክሊክ፤ እንዲሁም አድቬር ኤች-ኤፍ-ኤ፤ እና አድቬር ዲስከስ የአድቬር አይነቶች ምሳሌ ናቸው። አስተሻሸጋቸው እና አጠቃቀማቸው የተለያየ ቢሆንም በውስጣቸው የሚይዙት አንድ አይነት መድሃኒት ነው። **ይህ የአጠቃቀም መማሪያ የሚጠቅመው ለአድቬር ዲስከስ ብቻ ነው።**




## መድሃኒቱን ለመውሰድ

1. ምስሉ ላይ እንደሚታየው በግራ መደፍዎ የመድሃኒቱን እቃ አጋድመው ይያዙት። የመድሃኒቱን እቃ እፍ ለመክፈት **መሸፈኛውን በቀኝ እጅዎ ከራስዎ ተቃራኒ እቅጣጫ እስከመጨረሻው** ድረስ ይግፉት። ይህን ግዜ የመድሃኒቱ አፍ ይታያል።



2. የመድሃኒቱን አፍ ወደራስዎ ያዙሩት። ከመድሃኒቱ እቃ አፍ አጠገብ የምትገኘውን **መክፈቻ ከራስዎ በተቃራኒ አቅጣጫ ክሊክ የሚል ድምጽ እስከሚሰሙ ድረስ ያዙሩት። በዚህ ግዜ የመድሃኒቱ ዱቄት ቦታው ይገባል።** ከዚህ በሃላ የመድሃኒትን እቃ **እንደተጋደመ** ይያዙት። በሃይል ማንቀሳቀስ ቦታው የገባውን ዱቄት መድሃኒት እንዲፈስ ያደርገዋል።
3. መድሃኒቱን ከመሳቦ በፊት **የሚችሉትን ያህል ወደውጭ ይተንፍሱ።** ወደመድሃኒቱ እቃ አፍ እንዳይተነፍሱ ይጠነቀቁ።
4. የመድሃኒቱን እቃ አፍ በከንፈርዎ ገጥመው ይያዙና **በፍጥነት እና በጥልቀት ወደሳምባዎ ይተንፍሱ።** በአፍንጫዎ አይተንፍሱ።
5. የመድሃኒቱን እቃ አፍ ከአፍዎ ያውጡና **ለአስር ሰከንድ ወይም የሚችሉትን ያህል ትንፋሽዎን ይዘው ይቆዩ።** ከዚህ በሃላ በእርጋታ ወደውጭ ይተንፍሱ።
6. **የዲስከሱን ክዳን ወደቦታው ይመልሱ።** በትክክል መከደኑን የሚያውቁት **ክሊክ** የሚል ድምጽ ሲሰሙ ነው።
7. **አፍዎን በውሃ ይጉመጥመጡና ውሃውን ይትፉት።** ይህን ማድረግ ትረሽ የተባለ በሽታ አፎዎት ውስጥ እንዳይፈጠር ይከላከላል።
8. የመድሃኒቱን እቃ ማጽዳት አያስፈልግም። ሲያስቀምጡት ደረቅ ቦታ አጋድመው ያስቀምጡት።

https://www.gsksource.com/pharma/content/dam/GlaxoSmithKline/US/en/Prescribing_Information/Advair_Diskus/pdf/ADVAIR-DISKUS-PI-PIL-IFU.PDF#page=60


Rediet Yemane, PharmD